# አማራው የሌለው የት ሄዶ ነው?

**Solomon Derzie፣ ሐሙስ ሐምሌ 28 ቀን 2008 ዓም.**

**(https://www.facebook.com/search/top/?q=solomon%20derzie%20posts)**

ይህን ነገር በመለጠፌ አንዳንድ ሰዎች "አሁን ይህን ማንሳት ምን ይጠቅማል፣ለምን አስፈለገ" እና ሌላም እያሉ ነገሩን ሊያጣጥሉትና ጉዳዩን እንደ ቀላል ነገር ሊያሳንሱት ይፈልጋሉ፤ እነዚህ ሰዎች በአማራው ኪሳራ ኢትዮጵያ ነፃ እንድትወጣ የሚመኙ ናቸው። የነፕሮፌሰር መስፍንና ደቀመዝሙሮቻቸው፤ እንደ ይልቃል አይነቱና፣ ብዙዎቹ የአንድነት ኃይል ተብዬዎቹ የአማራውን ህልውና ክደው ይህን አስተሳሰብ በህዝብ ውስጥ በማስረፃቸው አማራው ተደራጅቶ ከግራም ከቀኝም የሚወርድበትን ውርጅብኝ እንዳይመከት አድርገውታል። በመሆኑም አማራው የደረሰበት ጉዳት ቀላል አይደለም።

በስማችሁ ፈንታ ጓደኞቿችሁ አንቺ ወይም አንተ ብለው ሲጠሯችሁ የምትናደዱ ሰዎች አማራው ማንነቱን ተክዶ 25 አመት ሙሉ ሲቀለድበት ቆይቶ አሁን ግን አማራ ነኝ ብሎ «ሆ» ብሎ በመነሳቱ ምን ያክል የስነልቦና መነሳሳትን እንዳስገኘለት እያያችሁ፤ «ምን ጥቅም አለው» እያላችሁ ነገሩን ለማሳነስ መሞከራችሁ የሚገርም ሆኖ ነው ያገኘሁት። አሁንም የትኩረት አቅጣጫውን ልታጣምሙና ድሉን ልትነጥቁት ይዳዳችኋል። አማራው ለዘመናት «አንተ ኢትዮጵያዊነት እንጂ በዘር መደራጀት አያምርብህም» እያሉ በማጃጃላቸው ጠላቶቹን በመጡበት መንገድ ተደራጅቶ ባለመመከቱ 5 ሚሊዮን አማራ ከምድረ ገፅ ጠፍቷል። ይህ ሲሆን ማንም የደረሰለት አልነበረም፣ እንኳን ሊከላከሉለት ቀርቶ ይደርስበት የነበረውን በደል በአግባቡ ሊዘግቡት አይፈልጉም ነበር።




የ40 ሚሊዮን ህዝብ ህልውና መካድ ያላሳሰባችሁ የነፕሮፌሰር መስፍን አምላኪዎች፤ከንግዲህ በአማራው ኪሳራ የአንድነት ተብዬው ንግድ አክትሟልና እርማችሁን አውጡ። ገና ምን አይታችሁ በአማራው ላይ የተፈፀመውን ክህደትም ሆነ እልቂት የሚያትት ጥንቃቄ በተሞላበት ተጠንቶ ብዙ የተለፋበት የስራ ውጤት "ምፅዓተ አማራ"ተብሎ የተሰየመ ከስድስት መቶ በላይ ገፅ ያለው መፅሃፍ በቅርብ ይወጣል። ያንን ሲያነቡ የአማራው ልጆች ምን ያክል ወንጀልና ደባ በንፁሃን ወገኖቻቸው ላይ እንደተፈፀመ ይገነዘባሉ። ይህን ግንዛቤ የጨበጠ አማራ ወደፊት ለሁለተኛ ጊዜ የጥቃት ሰለባ እንዳይሆን ይጠቅመዋል። አይሁዶችም ይህንኑ ነው እያደረጉ ያሉት። ትውልድ የማወቅ መብት አለው፣ ግዴታውም ነው።

ይህን ትልቅ ጉዳይ ነው የነ ይልቃል አዛኞች ልታሳንሱ የምትሞክሩት፣ በየዋህነት ከሆነ ነገሩን አቅላችሁ ያያችሁት ከንግዲህ እኛን ከመተቸቱና ለመምከር ከመሞከር ብትታቀቡ ደህና ነው። የምናደርገውን ጠንቅቀን እናውቃለን። አማራውን የትዬለሌ ከሆነው ረጅም እንቅልፉ እየቀሰቀስነው ነው። እግዚአብሄር ይመስገን፣ አማራውም እየነቃ ነው።